## አዋጅ ቁጥር -------/2016

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንብረት ማስመለስ አዋጅ

የኢኮኖሚ ወንጀል በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ ይህንን ወንጀል መከላከል እና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ እና ማንኛውም ሰው ከሕገ-ወጥ ድርጊት ማንኛውንም አይነት የኢኮኖሚ ጥቅም ማግኘት እንዳይችል የሚያደርግ ስርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፥

በወንጀል የተገኘ ንብረትን ማጥናት፣ መለየት፣ ማገድ፣ መያዝ፣ መመርመር፣ መክሰስ፥ ንብረት ማስተዳዳር እና መውረስን የሚመለከቱ በተለያዩ ሕጎች ተበታትነው የሚገኙ ድንጋጌዎች በአንድ የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ በማምጣት እና ለሁሉም የወንጀል አይነቶች እንዲያገለግሉ በማድረግ ለመሰረታዊ የሕግና የአፈጻጸም ጥያቄዎች ወጥነት ያለውና በቂ መልስ የሚሰጥ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ምንጩ ያልታወቀ ንብረት በሀገሪቱ የግብር ስርዓት፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የገንዘብ ዝውውር ስርዓት እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ በመሆኑእና ያለው የህግ ማዕቀፍ በመንግስት እና በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ችግሩን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

ኢትዮጵያ በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስን በተመለከተ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተግባር ለማስፈጸም እና በወንጀል ድርጊት የሚገኝ ንብረትን ማስመለስ፤ መውረስና ማስተዳደርን በተመለከተ ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን የሚያሟላ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 55 (1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

Draft-Confidential

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የንብረት ማስመለስ አዋጅ ቁጥር………/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) **"ንብረት"** ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ፣ የማይንቀሳቀስ፣ ገንዘብ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ሃብት ሲሆን በሃብቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም መኖሩን የሚያረጋግጥ እንደ ባንክ ክሬዲት፣ ትራቭለር ቼክ፣ የባንክ ቼክ፣ የክፍያ ትዕዛዝ፣ ምናባዊ ንብረት፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ አክሲዮን ወይም ቦንድ የመሰለ ማንኛውንም አይነት ሰነድ እና ከሃብቱ የተገኘን ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ገቢን ወይም ማናቸውንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ይጨምራል፤

2) **"የወንጀል ፍሬ"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ ማንኛውም ንብረት ሲሆን ይህንኑ ንብረት መሰረት አድርጎ የተገኘ ገቢ ወይም ትርፍ፣ ለወንጀል መፈጸሚያነት ከዋለ ንብረት የሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍን ይጨምራል፤

3) **"የወንጀል መፈጸሚያ"** ማለት በማንኛውም መንገድ በሙሉ ወይም በከፊል ለወንጀል ድርጊት መፈጸሚያነት የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ንብረት ነው፤

4) **"ተጎጂ"** ማለት በወንጀሉ ምንም ተሳትፎ ሳይኖረው በተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት ንብረቱን፣ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ወይም ጥቅም ያጣ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ሊሆን ይችላል፤

Draft-Confidential

5) **"ንብረት ማስመለስ"** ማለት በወንጀል ድርጊት ወይም ምንጩ ባልታወቀ ንብረት የተገኘን ወይም ግንኙነት ያለውን ንብረት ማጥናት፣ መለየት፣ ማገድ፣ መያዝ፣ መመርመር፣ በንብረት አስተዳዳሪ ስር ማቆየትና እንዲወረስ ማድረግ ነው፤

6) **"መውረስ"** ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የንብረት ባለቤትነት መብትን በዘላቂነት ማሳጣት ነው፤

7) **"በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ መውረስ"** ማለት ተከሳሹ በፍርድ ቤት በወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ በተወሰነ ጊዜ ውሳኔውን መሰረት በማድረግ የሚከናወን የንብረት መውረስ ነው፤

8) **"በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ መውረስ"** ማለት በማንኛውም አይነት ወንጀል በፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ ባይባልም በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከናወን የንብረት መውረስ ነው፤

9) **"ማገድ"** ማለት በፍርድ ቤት ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው ውሳኔ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ንብረቱ እንዳይተላለፍ፣ ወደሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ መከልከል ነው፤

10) **"መያዝ"** ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው ውሳኔ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ንብረቱ እንዳይተላለፍ፣ ወደሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከልና በዐቃቤ ሕግ ወይም በንብረት አስተዳዳሪ ቁጥጥር ወይም ይዞታ ስር እንዲተዳደር ማድረግ ነው፤

11) **"ምናባዊ ንብረት"** ማለት በዲጂታል መንገድ ለመገበያየት፣ ለማስተላልፍ ወይም ለኢንቨስትመንት ክፍያ ሊያገለግል የሚችል ሲሆን በዲጂታል የሚወከሉ የመገበያያ ገንዘብን፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ሌሎች ተላላፊ የሆኑ የክፍያ ሰነዶችን አይጨምርም።

12) **"ጠቋሚ"** ማለት በወንጀል ድርጊት ከተገኘ ንብረት ወይም ምንጩ ባላታወቀ ንብረት ጋር በተያያዘ በምርመራ ወይም በክስ ሂደት መረጃ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ ሰው ነው፤

Draft-Confidential

13)**“መርማሪ”** ማለት የንብረት ማስመለስ ምርመራ ስራን የሚሰራ ባለሙያ ነው፤

14)**“ዐቃቤ ሕግ” ማለት** በሚኒስቴሩ ውስጥ በዐቃቤ ሕግነት ሙያ የተቀጠረ እና የንብረት ማስመለስ ምርመራ እና ክስር ስራን የሚሰራ ባለሙያ ነው፥

15) **“የንብረት ምርመራ”** ማለት ንብረት ለማስመለስ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

16) **“ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር”** ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የፍትህ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

17) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

18) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ፦

1) በወንጀል ህጉ ወይም በሌሎች ሕጎች መሰረት ወንጀሉን መክሰስ የኢትዮጵያ ስልጣን በሆነ ጊዜ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረትን ለማስመለስ ዓላማ ፤ ወይም

2) ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማስመለስ ሂደት ላይ፤

ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማትን በተመለከተ**

1) የወንጀል ሕግ ድንጋጌ አንቀፅ 34 ቢኖርም የመንግስት ተቋማትን ሳይጨምር የሕግ ሰውነት ያለው ማንኛውም ድርጅት በማንኛውም ሁኔታ በወንጀል ድርጊት አማካኝነት ንብረት ማግኘቱ ወይም ለሌላ ሰው ማስገኘቱ ወይም በሌላው ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት ስለማድረሱ ጠቋሚ ማስረጃ ከተገኘ የንብረት ማስመለስ ሂደቱ በዚህ ሕግ መሰረት ይመራል፤

Draft-Confidential

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በተመለከተ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተቋማትና ድርጅቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ስለማስመለስ

### 5. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ድንጋጌዎች ላይ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ሃላፊነት ያለባቸው አካላት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው፡-

1) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለው ንብረት ወይም የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ የማይመጣጠን እንደሆነ እና የንብረቱን ወይም የኑሮ ደረጃውን ምንጭ በተመለከተ ምክንያታዊ የሆነ የወንጀል ጥርጣሬ በኖረ ጊዜ የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ ወይም ያለው ንብረት እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር ንብረቱ ይወረሳል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ህጋዊ ገቢ እንዳለው የሚያስረዳ የተመዘገበበት ስርዓት የሌለው ወይም ገቢው አነስተኛ በመሆኑ ከግብር ነጻ የሆነ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለው ንብረት ወይም የኑሮ ደረጃው ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ የማይመጣጠን እንደሆነ የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ ወይም ያለው ንብረት እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር ንብረቱ ይወረሳል፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ ዓላማ “በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያፈራው ንብረት” ማለት በራሱ ስም የሚገኝ ንብረት፣ በራሱ ስም ባይሆንም ለራሱ ጥቅም ሲያዝበት ወይም ሲቆጣጠረው የነበረው ንብረት፣ የተጠቀመው ወይም ያስወገደው

Draft-Confidential

ንብረት፣ በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ያስተላለፈውን ንብረት ይጨምራል፡፡

## 6. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የቅድመ ክስ ሥርዓት

1) ዐቃቤ ሕግ ምንጩ ያልታወቀ ነው ብሎ የጠረጠረውን ማንኛውንም ንብረት ዝርዝር እና የተገኘበትን አግባብ የሚያሳይ መግለጫ እንዲያቀርብ በፅሁፍ ጥያቄ የቀረበለት ማንኛውም ሰው ጥያቄው በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለዐቃቤ ህግ ዝርዝር ማስረጃዎችን በማያያዝ በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፤
2) የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው የንብረቱን ምንጭ ለማስረዳት የሚያቀርበው ማስረጃ ህጋዊ መሆን አለበት፤
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ማስረጃዎችን ለማቅረብ የተመለከተው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር ለዐቃቤ ህግ በሚቀርብ አቤቱታ ሊራዘም ይችላል፥ ሆኖም ይህ የጊዜ ገደብ ከስድስት ወር ሊበልጥ አይችልም፤
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ዝርዝር ማስረጃ እንዲያቀርብ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረበ ንብረቱ ምንጩ ያልታወቀ ነው የሚል ግምት ተወስዶበት ዐቃቤ ህግ ንብረቱ እንዲወረስ ክሱን ለፍርድ ቤት ያቀርባል፤
5) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረቡ ዝርዝር ማስረጃዎች ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን የተመለከተ ክስ ሲቀርብ በፍርድ ቤት ማስረጃ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 7. በራስ ላይ ማስረጃ ስለማቅረብ

1) የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው የንብረቱን ምንጭ ለማስረዳት የወንጀል ሃላፊነት የሚያመጣበት ማስረጃ ቢሰጥም በወንጀል ችሎት በራሱ ላይ ማስረጃ ሆኖ አይቀርብም፤
2) የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው ሀሰተኛ ማስረጃ ካቀረበ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተሰጠውን መብት መጠቀም አይችልም፤

Draft-Confidential

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ የተፈጸመውን ወንጀል በሌሎች ማስረጃዎች ከማስረዳት አይከለክልም፡፡

## 8. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ክስ የሚቀርብበት ጊዜ እና የገንዘብ መጠን

1) ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት ባሉት አስር ዓመት ውስጥ ወይም ተፈፃሚ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ለማስመለስ በዚህ አዋጅ መሰረት ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ክስ ሊቀርብ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አዋጁ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት ባለው አስር ዓመት ውስጥ በተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ላይ ክስ የሚቀርበው ምንጩ ያልታወቀው የንብረቱ ግምት ከብር አስር ሚሊዮን በላይ ከሆነ ነው፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለንብረት ምርመራ

## 9. የንብረት ምርመራ አጀማመር

ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ በተሟላ ጊዜ በዓቃቤ ሕግ ወይም በመርማሪ የንብረት ማስመለስ ምርመራ ይጀመራል፡-

1) በሕግ የወንጀል ምርመራ ስልጣን ከተሰጣቸው ተቋማት ወይም ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት በሚመጣ ጥቆማ ወይም መረጃ፤

2) መረጃ ያለው ማንኛውም ሰው በሚሰጠው ምክንያታዊና አሳማኝ ጥቆማ፤

3) ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ወይም ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት በሚቀርብ ጥቆማ ወይም መረጃ ፤ ወይም

4) በማንኛውም ሁኔታ የንብረት ማስመለስ ምርመራ ሊጀመር የሚችልበት በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን።

Draft-Confidential

## 10.ጠቅላላ የንብረት ምርመራ ዘዴ

በወንጀል ስነ-ሥርዓት ሕግ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች የምርመራ ዘዴን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ የንብረት ምርመራ በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተሉትን የምርመራ ዘዴዎች ሊጠቀም ይችላል፡-

1) የገንዘብ ፍሰት ሰነዶችና ምናባዊ ንብረት ምርመራ፣

2) የቀረጥና የግብር ሰነዶች ምርመራ፣

3) የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰነዶች ምርመራ፣

4) የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሪል እስቴትን የሚመለከት ማንኛውም ምርመራ፣

5) የጉዞ ሰነዶች፣ የፓስፖርት ወይምየወሳኝ ኩነቶች ሰነድ ምርመራ፣

6) የሃብት ምዝገባ ሰነዶች ምርመራ፣

7) የካፒታል ገበያ መረጃዎች ምርመራ፤ ወይም

8) ሌሎች ለንብረት ማስመለስ ሊያገለግሉ የሚችሉ ማናቸውንም የምርመራ ዘዴዎች፣

## 11.ልዩ የንብረት ምርመራ ዘዴ

1) የወንጀል ፍሬ ወይም ከወንጀል ድርጊት ጋር የተገናኘ ማንኛውም ንብረት መኖሩን የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ አግባብነት ካለው ተቋም ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ልዩ የምርመራ ዘዴዎች በመጠቀም ማስረጃ ለመሰብሰብ ይችላል፡-

ሀ) በባንክ ሂሳቦችና በሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦች ላይ ክትትል በማድረግ፤

ለ) የኮምፒውተር ሥርዓቶችን፣ መረቦችንና ሰርቨሮችን በማየት ወይም በመድረስ፤



Draft-Confidential

ሐ) በፖስታ፣ በደብዳቤ፣ በቴሌፎን፣ በፋክስ፣ በራድዮ፣ በኢንተርኔት ወይም በሌሎች ማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች ወይም መሣሪያዎች የሚደረጉ ልውውጦችን ወይም ግንኙነቶችን በክትትል ስር በማዋል ወይም በመጥለፍ፤

መ) ድርጊቶችን፣ የኑሮ ዘይቤውን፣ ንግግሮችን በድምጽ ወይም በምስል በመቅረጽና ፎቶግራፍ በማንሳት፤

ሠ) በሽፋን ውስጥ የሚደረግ ምርመራ በማድረግ፤

ረ) በቁጥጥር ውስጥ የሚደረግ ምርመራ በማድረግ፤

2) ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተደነገጉ ልዩ የማስረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚችለው ፍርድ ቤት የምርመራውን አስፈላጊነት ሲፈቅድ ብቻ ነው፤

3) ፍርድ ቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ለቀረበ ጥያቄ የሚፈቀደው ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪው በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ሊገኙ የማይችሉ ማስረጃዎች መሆናቸውን የሚጠቁም ምክንያት መኖሩን ለፍርድ ቤቱ ሲያስረዳ ነው፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመው ለሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ ለወከለው ኃላፊ በማስፈቀድ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በልዩ የንብረት ምርመራ ዘዴ ማስረጃ ሊሰበስብ ይችላል፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በልዩ የንብረት ምርመራ ዘዴ ማስረጃ ለመሰብሰብ በተጀመረ በ48 ሰዓት ውስጥ ምክንያቶቹንና የተሰጠውን ጊዜያዊ ፈቃድ ጨምሮ ለፍርድ ቤት በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፤ ፍርድ ቤቱም የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል፡፡

Draft-Confidential

## 12.ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም እንዲገለጽ የመጠየቅ ሥልጣን

1) ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ከወንጀል የተገኘ ንብረት ወይም ለወንጀል ድርጊት መፈጸሚያነት የዋለ ንብረት ስለመኖሩ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው በማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ይዞታ ወይም ባለቤትነት ስር የሚገኝ ንብረትን በተመለከተ ማንኛውም ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም እንዲገለጽለት በፅሁፍ ሊጠይቅ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የሚጠየቀው ማስረጃ ወይም እንዲገለጽ የተፈለገው ጉዳይ የሚገኘው በማንኛውም የመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ተቋም ውስጥ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪው ይህንኑ ማስረጃ መጠየቅ ይችላል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) መሰረት ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ስለተጠየቀው ነገር እንዲገልጽ የሚጠየቅ ማንኛውም ሰው፥ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ማስረጃው በሚገኝበት ሁኔታ የማቅረብ ወይም የመግለፅ ግዴታ አለበት፤

4) ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም እንዲገለጽለት የሚያቀርበው ጥያቄ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል ፦

ሀ/ ማስረጃ የተጠየቀው አካል በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ እንዲያቀርብ፤

ለ/ ለቀረቡለት ጥያቄዎች መልሱን በተወሰነ ጊዜና ቦታ እንዲመልስ፤

ሐ/ ማንኛውም የሚፈለግ ማስረጃ በይዞታው የሚገኝ አካል በይዞታው የሚገኙ ሰነዶችን፣ መዛግብቶችን፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎችን በመርማሪው አካል እንዲታዩ እንዲመረመሩ ወይም ከዋናው ማስረጃ ጋር የተገናዘበ ቅጅ እንዲያቀርብ፤

## 13.መረጃ አሳልፎ መስጠትን ስለመከልከል

1) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው አግባብ ስራውን ሲያከናውን ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ማስረጃ፥



Draft-Confidential

ሀ/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው ሁኔታ ስራውን በተገቢው መንገድ ለማከናወን እንዲረዳው ካልሆነ፥

ለ/ በፍርድ ቤት ካልታዘዘ፥ ወይም

ሐ./ ከሚኒስትሩ የጽሁፍ ፍቃድ ካላገኘ፥

በስተቀር ለማንኛውም ሰው መግለጽ ወይም አሳልፎ መስጠት አይችልም፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተደነገገውን ክልከላ የተላለፈ ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

## 14. የማስረጃ ምዘና ሥነ-ሥርዓት

1) በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም አይነት የንብረት ማስመለስ ወይም ውርስ ጉዳይ የሚታየው በፍትሐ-ብሄር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ሲሆን የማስረዳት ምዘናው በፍትሃብሄር ክርክር ጊዜ እንደሚቀርበው የማስረጃ ደረጃ ይሆናል፤

2) በወንጀል ምርመራ ወይም በወንጀል ፍርድ ሂደት የተገኘ ማስረጃ ለንብረት መውረስ ዓላማ በማስረጃነት ይቀርባል፤

3) በወንጀል ክርክር ሂደት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በዚህ ሂደት የቀረበ ማስረጃ በድጋሚ የማስረጃ ምዘና ሂደት ማለፍ ሳያስፈልገው የንብረት ማስመለስ ክርክሩን ለሚመለከተው ችሎት ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ ሆኖ ይቆጠራል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ክርክሩ ያልተካተቱ ተጨማሪ ማስረጃዎች ለንብረት ማስመለስ ክርክር ከማቅረብ የሚከለክል አይሆንም ፡፡

Draft-Confidential

## ክፍል አራት

## ስለንብረት ማገድ ወይም መያዝ

### 15. ስለማገድ ወይም መያዝ

1) የንብረት መውረስ ሊያስከትል የሚችል ምርመራ እየተካሄደ ከሆነ፣ ክስ ከቀረበ፣ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ወይም ሌላ በቂ የሆነ ምክንያት ሲኖር ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ንብረቱ እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፤

2) ሚኒስትሩ ወይም በሚኒስትሩ የሚወከል ሃላፊ የሚታገደው ንብረት በተፋጠነ ሁኔታ ሊሸሽ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ሊያሳጣው የሚችል ድርጊት መኖሩን ሲያምንበት ንብረቱን ለሶስት የሥራ ቀናት እንዲታገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ባሉት ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ የፍርድ ቤት ዕግድ ካልተጠየቀ ትዕዛዙ በራሱ ጊዜ ቀሪ ይሆናል፤

4) ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በተጠቀሰው ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ የፍርድ ቤት እግድ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ አቤቱታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ የእግዱ ትዕዛዝ ፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ እንደጸና ይቀጥላል፤

5) ዓቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት ለፍርድ ቤት የቀረበውን የእግድ አቤቱታ ትዕዛዝ ለተቀበለው ተቋም ያሳውቃል፤

6) የማገድ ትዕዛዝ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ይወስናል፤

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) ድንጋጌ ስር በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሰጠ ተገቢ ነው ብሎ ለሚወስነው የጊዜ ገደብ ተጨማሪ የእግድ ጊዜ ሊሰጥበት ይችላል፡፡

Draft Confidential

## 16.ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ የሚጠየቅበት ሁኔታ

1) ንብረት ለማስመለስ በሚደረግ ሂደት በሚከተሉት ምክንያቶች ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ንብረቱ ታግዶ እንዲቆይ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡-

ሀ/ ንብረቱ በማንኛውም ሰው ይዞታ ውስጥ ቢቆይ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት የማይኖር ከሆነ፣

ለ/ ለንብረቱ ኢኮኖሚያዊ ጥበቃ የተሻለ እንደሆነ፥ ወይም

ሐ/ በንብረቱ ልዩ ባህሪ ምክንያት ባለበት መቆየቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

Draft Confidential

2) ንብረት ለመውረስ ወይም ለማስመለስ በሚደረግ ሂደት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ንብረቱ እንዲያዝ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡-

ሀ/ ተጠርጣሪው በታገደው ወይም በሚያዘው ንብረት ላይ ጉዳት ያደርሳል፣ ንብረቱን ይሰውራል ወይም ተጨማሪ ወንጀል ሊፈጽምበት ይችላል ተብሎ ሲታመን ፣

ለ/ ንብረቱ የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ለወንጀል መፈጸሚያነት የዋለ ስለመሆኑ ለመጠርጠር የሚያስችል ጠቋሚ ማስረጃ ሲኖር፣

ሐ/ ከወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ንብረት ባልተገኘ ጊዜ ወይም ቀድሞ የሸሸ እንደሆነ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚወረሰው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ህጋዊ ንብረት ሲገኝ፣

መ/ በሚሰጥ የእግድ ትዕዛዝ መሰረት ንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችል ማንኛውንም አይነት ጉዳት መከላከል የማይቻል በሆነ ጊዜ፣

3) የንብረት የማገድ ወይም የመያዝ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ በተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ስም ከሚገኝ ንብረት በተጨማሪ በትዳር ጓደኛ፣ ሳይጋቡ

እንደባልና ሚስት በሚኖሩ ሰዎች መካከል ወይም በልጆች ስም የሚገኝ ተመጣጣኝ ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡

4) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ግለሰብ የሚገኝ ንብረት በወንጀሉ ከተገኘው ንብረት ጋር ወይም ለወንጀል መፈጸሚያው ከዋለው ንብረት ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑ ከጠረጠረ የግለሰቡ ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

## 17.ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ የሚቀርብ ማመልከቻ አቀራረብና ይዘት

Draft-Confidential

ንብረት የመያዝ ወይም የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ ፤

1) የንብረት ምርመራው ፍሬ ነገርና በየደረጃው የተወሰዱትን እርምጃዎች፤ ክስ ያልተመሰረተ ከሆነ ጉዳዩ የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ፣

2) የሚያዘው ወይም የሚታገደው ንብረት ተፈጽሟል በተባለውና ምርመራ በተጀመረበት ወንጀል አማካኝነት ተጠርጣሪው ያገኘው የወንጀል ፍሬ፣ የወንጀል መፈጸሚያ ንብረት፣ ወይም የደረሰ ጉዳትን በሚመለከት አሳማኝ ምክንያት፤

3) የሚታወቅ በሆነ ጊዜ የንብረቶችን ዝርዝር አድራሻ፣

የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 18.ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ በቀረበ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ትዕዛዝ

1) ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት የቀረበውን ማመልከቻ መርምሮ፡-

ሀ/ ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲታገድ፣

ለ/ ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል በሚኒስቴሩ ስር እንዲሆን ወይም እንዲያዝ፤

ሐ/ አስተዳዳሪ እንዲሾም፥ ወይም

መ/ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ውሳኔዎች፣

ሊሰጥ ይችላል፤

2) ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ መሰረት የሚሰጠውን ትዕዛዝ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በንብረቱ ላይ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ላለው ሰው ያሳውቃል፡፡

## 19.የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ስለመመዝገብ

በንብረቱ ላይ ያለ መብት እንዲመዘገብ የሚያስገድድ ሕግ ያለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ንብረቱን የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ተቋም ትዕዛዙ እንደደረሰው ዝርዝር ይዘቱን ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት፡፡

## 20.የእግድ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 18 በተደነገገው መሠረት በንብረቱ ላይ የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ፥ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በተጠርጣሪው ላይ ከንብረቱ ጋር በተያያዘ የተጠረጠረበት የወንጀል ክስ ወይም ንብረቱን የማስወረስ ክስ ካልቀረበ የተሰጠው የመያዝ ወይም የእግድ ትዕዛዝ ቀሪ እንዲሆን ባለንብረቱ ወይም ተጠርጣሪው ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፥

2) ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የቀረበው ማመልከቻ ላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ እና አስተያየቱን በማገናዘብ የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዙ እንዲነሳ ሊወስን ይችላል ፤

3) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቢኖርም የንብረቱ ተይዞ ወይም ታግዶ መቆየት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ባመነበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ

Draft-confidential

ተገቢ ነው ለሚለው ተጨማሪ ጊዜ ንብረቱ ታግዶ ወይም ተይዞ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡

## 21. ስለ ማገድ እና መያዝ ይግባኝ

1) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ፍርድ ቤቱ በንብረቱ ላይ የሰጠውን የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል በወሰነ ጊዜ፥ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው፥

2) ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ይግባኝ የጠየቀ እንደሆነ፥ ንብረቱ እንዳይለቀቅ ይግባኝ ስለመጠየቁ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ይግባኝ የጠየቀበትን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፥ ፍርድ ቤቱም ማስረጃው እንደደረሰው የመያዝ ትዕዛዝ ይግባኙ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ቀድሞ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ጸንቶ ይቆያል፥

3) ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ  ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ይግባኝ ስለመጠየቁ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ማስረጃ ካልቀረበለት የተያዘው ወይም የታገደው ንብረት እንዲለቀቅ ይወስናል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት የተቀመጠው የአምስት ቀን የጊዜ ገደብ የሚቆጠረው ዐቃቤ ህግ የውሳኔው ግለባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ነው።

## 22. የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የማይሰጥበት ንብረት

1) በዚህ አዋጅ ስለንብረት ማገድና መያዝ የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ/ የተጠርጣሪው፣ የተከሳሹ፤ የፍርደኛው ወይም በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት የእለት መተዳደሪያ ወይም ሙያዊ ስራ ለመስራት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች፤

Draft-Confidential

ለ/ ለተጠርጣሪው፣ ለተከሳሹ፥ ለፍርደኛው ወይም በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት የዕለት ኑሮ ጠቃሚ የሚሆኑ እና ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ በልዩ ሁኔታ ለሚወስነው ጊዜ የሚሆን ስንቅ፤

እንዳይታገድ ወይም እንዳይያዝ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠርጣሪው፣ ተከሳሹ፥ ፍርደኛው ወይም በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆኑና የሚተዳደሩት ከተያዘው ወይም ከታገደው ንብረት በሚገኝ ገቢ ከሆነ ከታገደው ወይም ከተያዘው ንብረት ላይ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ለተከሳሹና በእርሱ ስር ለሚተዳደሩ ጥገኞች ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ የሚገምተውን ያክል ገቢ እየተቀረጠ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) የተደነገገውድንጋጌ ቢኖርም በተለየ ሁኔታ ውድ ከሆኑ ማዕድናት ወይም ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው የዕደጥበብ ስራዎች የተሰሩ ማናቸውም ቁሳቁሶች እንዲታገዱ ወይም እንዲያዙ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

4) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በሚያቀርበው በቂ ማስረጃ መሠረት ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን የሚያሳይ በሆነ ጊዜ ተጠርጣሪው፥ ተከሳሹ ወይም ፍርደኛው ከወንጀል ፍሬው የመጠቀም መብት አይኖረውም፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ንብረት መውረስ

### 23. ጠቅላላ ድንጋጌ

1) ከወንጀል ድርጊት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገናኘ ማንኛውም ንብረት፣ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ዝርዝር ድንጋጌዎች መሰረት ይወረሳል፤

Draft Confidential

2) በወንጀል ሕግ እና በሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎች መሰረት የንብረት መወረስ እንደ ቅጣት ያልተቀመጠባቸው የወንጀል ድርጊቶች ቢኖሩም ማንኛውም ሰው ከድርጊቱ የንብረት ጥቅም ስለማግኘቱ፣ ለሌላ ሰው ስለማስገኘቱ ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ስለማድረሱ ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ መሰረት የንብረት ማስመለስና መወረስ ሂደቱ ተፈጻሚ ይሆናል፥

3) በዚህ አዋጅ ስለንብረት መውረስ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወንጀል ድርጊቱ የንብረት ጥቅም ያገኘ፤ ያስገኘ ወይም ጉዳት ያደረስ ማንኛውም ሰው በድርድር ያገኘውን ጥቅም የሚመልስበትን ወይም ጉዳቱን የሚክስበትን ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 24. በንብረት መውረስ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት

1) በአንድ የወንጀል ድርጊት የተሳተፉ ሰዎች የንብረት መውረስ ማመልከቻ የሚቀርብባቸው በሆነ ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ወይም ለተገኘው ያልተገባ ጥቅም ከእያንዳንዳቸው የሚወረስ ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከእያንዳንዳቸው ለማስመለስ በቂ ንብረት ለማግኘት ባልተቻለ ጊዜ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) በተደነገገው መሰረት ንብረቱ የተወረሰበት ሰው ሌሎች የወንጀሉ ተሳታፊዎች ድርሻቸውን እንዲከፍሉ መጠየቅ ይችላል፡፡

Draft Confidential

## 25.ስለሚወረስ ንብረት

1) በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ ወይም በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት መውረስ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት፡-

ሀ/ የወንጀሉ ፍሬ የሆነ ንብረት፣ የወንጀሉ ፍሬ ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ንብረት፤

ለ/ ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘ ገቢና ሌሎች ጥቅሞችን የሚመለከት ንብረት፤

ሐ/ ለወንጀሉ መፈጸሚያነት የዋለ ንብረት ወይም ከዚህ ንብረት የተገኘ ገቢ ወይም ትርፍ

መ/ ባለቤትነቱ የተላለፈለት ሰው ቅን ልቦና እንደተጠበቀ ሆኖ፤

I. ንብረቱን፣

II. የወንጀሉን ፍሬ ወይም ተመጣጣኙን፣

III. ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ንብረትን፣

IV. ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘ ገቢን ወይም ለወንጀሉ መፈጸሚያነት የዋለ ንብረትን

ከመወረስ ለማዳን በማሰብ ለማንኛውም ወገን የተላለፈ ንብረት፤

ሠ/ ከወንጀሉ ፍሬ እንዲሁም ከዚሁ የወንጀል ፍሬ የተገኘ ገቢ፣ ከወንጀል ፍሬው ጋር ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ ከተገኘው ንብረት ወይም ለወንጀል መፈጸሚያነት ከዋለ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ ግምት ያለው የወንጀል ፈጻሚው ንብረት፤

በቀረበለት ማመልከቻ መሰረት እንዲወረስ ይወስናል፤

2) እንዲወረስ ማመልከቻ በቀረበበት ወይም ውሳኔ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት አለኝ በሚል ማመልከቻውን ወይም ውሳኔውን ለመቃወም ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በንብረቱ ላይ መብት ሲተላለፍለት ምንጩ ህገ-ወጥ መሆኑን ሳያውቅና ተገቢ የሆነ ዋጋ ከፍሎበት ወይም ለሰጠው ተመጣጣኝ አገልግሎት ታስቦለት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የንብረቱን መወረስ ሊያስቀረው አይችልም፤

3) ማንኛውም በወንጀል የተፈረደበት ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የያዘው እና በወንጀሉ ከመሰከሱ አስቀድሞ ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተገኘ ንብረት ጥፋተኛ የተሰኘበት ወንጀል ውጤት ነው ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት

Draft-Confidential

ካለና ግለሰቡ በህጋዊ መንገድ ያፈራው ስለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ካልቻለ በተጨማሪነት እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፤

4) ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የንብረቱን መወረስን ለማስቀረት ዓላማ የተደረገ ማንኛውንም ሕጋዊ ሰነድ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ማድረግ ይችላል፤ ሆኖም ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገው ሰነድ የተፈረመው ዋጋ በተከፈለበት ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ከሆነ በቅን ልቦና ክፍያ የፈፀመው ተዋዋይ ወገን የከፈለው ገንዘብ ብቻ ከሚወረሰው ንብረት ላይ ተመላሽ ይደረግለታል፤

5) በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የወንጀል ጉዳዩ ተከሳሽ በመጥፋቱ ምክንያት የወንጀል ክሱ መቀጠል የማይችል በሆነ ጊዜ ወይም ተጠርጣሪው በመጥፋቱ ምክንያት የወንጀል ክስ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ የንብረት ማስመለስ ሂደቱን በሕግ ወኪሉ ወይም በጠበቃ ተወክሎ ለመከራከር አይችልም፤

6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሠ) መሰረት ከወንጀል ፍሬው ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ ንብረት የሚወረሰው ተቀላቅሎ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል፤

7) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (7) ድንጋጌ ቢኖርም ከወንጀል ፍሬው ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ ንብረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊወሰን ይችላል፡-

ሀ. በወንጀል የተገኘው ንብረት ከህጋዊ የንብረት መጠን ጋር ተመጣጣኝ ዋጋ ሲኖረው፥

ለ. በወንጀል የተገኘው ንብረት ለህጋዊው ንብረት አይነተኛ ሚና ያለው ሲሆን ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ለንብረቱ ዋና ክፍል ሲሆን ወይም

ሐ. በወንጀል የተገኘውን ንብረቱን ህጋዊ ለማስመሰል የተጠቀመበት እንደሆነ።

**26.ንብረት ለማስወረስ ማመልከቻ በድጋሚ ስለማቅረብ**

Draft Confidential

1) የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ በቀረበበት ተከሳሽ ላይ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ወይም ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ማንኛውም ከወንጀል ድርጊቱ ጋር የሚገናኝ ንብረት የተገኘ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ አዲስ የተገኘውን ንብረት በተመለከተ አዲስ የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ ያቀርባል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር በተደነገገው መሰረት ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት አዲስ የተገኘው ንብረት የመጀመሪያው ማመልከቻ ሲቀርብ አብሮ ለማቅረብ የሚያስችል ማስረጃ ባለመኖሩ ወይም በማናቸውም በቂ ምክንያት መሆኑን ሲያረጋግጥ ማመልከቻውን ይቀበላል፡፡

## 27.ከክስ ነጻ የሚደረግ ምስክር ንብረትን ስለማስመለስ

1) በሌሎች ሕጎች በሚወጡ ድንጋጌዎች መሰረት ከክስ ነጻ የሚደረግ እና በወንጀል ክርክር ሂደቱ ወደ ምስክር የዞረ የወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው በወንጀል ድርጊቱ ያገኘው ንብረት እንዲመልስ ወይም ያደረሰው ጉዳት እንዲክስ ይደረጋል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ጥፍተኝነት ድርድር ላይ የሚደረጉ ስምምነቶችን አይመለከትም።

## 28.በውርስ ላይ ይግባኝ ስለማቅረብ

1) ፍርድ ቤት በሚሰጠው የንብረት መውረስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለሚመለከተው የበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፤

2) ፍርድ ቤቱ የታገደው ወይም የተያዘው ንብረት እንዳይወረስ በሚል የወሰነ እንደሆነ እና ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ አስቀድሞ የተሰጠው የዕግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ይግባኙ ወይም አቤቱታው የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጸንቶ ይቆያል፤

3) ፍርድ ቤቱ የታገደው ወይም የተያዘው ንብረት እንዳይወረስ የወሰነ እንደሆን ዐቃቤ ህጉ ይግባኝ መጠየቁን የሚያስረዳ የጽሁፍ ማስረጃ በአስረ አምስት ቀን

Draft-Confidential

ውስጥ ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ካላመጣ በቀር ንብረቱ እንዲለቀቅ ይወስናል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት የተቀመጠው የአስረ አምስት ቀን የጊዜ ገደብ የሚቆጠረው ዐቃቤ ህግ የውሳኔው ግለባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ነው።

29.በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ የንብረት መውረስ

1) ማንኛውም ሰው በወንጀል ክስ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ እና ከወንጀል ድርጊቱ ንብረት ያገኘ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ንብረት እንዲወረስ ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ያቀርባል፤

2) የወንጀል ቅጣቱ በይቅርታ ወይም በምህረት ቀሪ የተደረገለት፥ የተገደበለት ወይም በአመክሮ የተለቀቀ ማንኛውም ሰው፥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ለሚቀርብ የንብረት ማስመለስ ሂደት መቃወሚያ አድርጎ ማቅረብ አይችልም፤

3) ጥፋተኛ በተባለ ሰው ላይ የንብረት መውረስ ማመልከቻ የሚቀርበው ለወንጀል ቅጣት አፈጻጸም በወንጀል ሕግ ወይም በሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎች በተቀመጠው የይርጋ የጊዜ ገደብ መሰረት ይሆናል፤

4) ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ በቀረበለት ማመልከቻ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ባለው ማንኛውም ጊዜ ፍርድ ቤቱን በማስፈቀድ ማመልከቻውን ለማሻሻል ይችላል፡፡

30.በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት መውረስ

1) ማንኛውም ሰው በወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ባይሰጥበትም ከድርጊቱ የንብረት ጥቅም ያገኘ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ንብረት እንዲወረስ ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ያቀርባል፡፡

Draft-Confidential

2) በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት መውረስ ማመልከቻ የሚቀርበው ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በተሟላ ጊዜ ነው፡-

ሀ/ በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው ሰው ሲሞት፣ ሲያመልጥ፣ ሲጠፋ ወይም ወንጀል ፈጻሚው ሳይታወቅ ሲቀር፤

ለ/ በይርጋ ምክንያት የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ ማሰጠት ሳይቻል ሲቀር፤

ሐ/ የተገኘው ማስረጃ በወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማሰጠት የወንጀል የማስረጃ ምዘና መስፈርትን የማያሟላ ሲሆንና ከወንጀል ድርጊቱ ጥቅም ስለመገኘቱ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር፤

መ/ በወንጀል ምርመራ ሂደት የተገኘው ማስረጃ ለወንጀል ስነ-ሥርዓት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ወይም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ ከቀረበበት የወንጀል ክስ ነጻ የተባለ እንደሆነ፤

ሠ/ ተከሳሹ ምህረት ሲደረግለት ወይም የቀረበበት ክስ በማንኛውም ምክንያት ሲቋረጥ፤

ረ/ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገናኝ እና በሶስተኛ ወገን ይዞታ ወይም ባለቤትነት ስር የሚገኝ ንብረት ሲሆን፤

ሰ/ ተጠርጣሪው በወንጀል ያለመከሰስ መብት ያለው ሲሆን፤

ሸ/ የመንግስትና የሃይማኖት ተቋማትን ሳይጨምር የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ተቋማት ከወንጀል ድርጊታቸው ንብረት ያገኙ ሲሆን እና በወንጀል የማይከሰሱበት ሁኔታ ሲኖር፤

ቀ/ ከክስ ነጻ ተደርጎ ወደ ምስክርነት የዞረ እና በድርጊቱ ያገኘውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ሲያጋጥም።

Draft Confidential

## ክፍል ስድስት

## ስለ ንብረት ማስተዳደር

### 31. ንብረት አስተዳዳሪ ስለመሾም

`ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት፣ በዐቃቤ ሕግ፣ በመርማሪ ፣ በተጠርጣሪው ወይም በንብረቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ሶስተኛ ወገን ጠያቂነት በዚህ ሕግ መሰረት የተያዘ ንብረት በንብረት አስተዳዳሪ ስር እንዲቆይ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት የንብረት አስተዳደር መሾም ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን የንብረት አስተዳደር እንዲሾም ለማዘዝ ይችላል፡፡

### 32.ንብረት አስተዳዳሪ ስለሚመረጥበት ሁኔታ

1) ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ሰው የንብረት አስተዳዳሪ ሆኖ ሊሾም ይችላል፤

2) ፍርድ ቤት የንብረት አስተዳዳሪ ሲሾም በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሌለ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፤

3) ፍርድ ቤቱ የንብረት አስተዳዳሪ በሚሾምበት ሂደት የዐቃቤ ሕግን እና የሚቻል በሆነ ጊዜ የንብረቱን ባለመብቶች አስተያየት መስማት አለበት፡፡

Draft-Confidential

### 33.የንብረት አስተዳዳሪው ተግባርና ኃላፊነት

1) በዚህ አዋጅ መሰረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዘ ንብረትን እንዲያስተዳድር የተሾመ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ እንደንብረቱ አይነትና ሁኔታ በህግ አግባብ የንብረቱን ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ ጥቅም በተሻለ ለመጠበቅ ምክንያታዊ እና ተገቢ የሆነ ማንኛውንም የአስተዳደር ሥራ ይሰራል፤

ለ/ በአስተዳዳሪነት የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ የመክሰስ እና የመከሰስ መብት ይኖረዋል፤

ሐ/ ከንብረቱ የሚገኝ ኪራይ፣ ትርፍ ወይም ሌላ ማንኛውንም ገቢ ይሰበስባል፤

መ/ ንብረት አስተዳዳሪው ንብረቱን መያዣ ከማድረግ እና ወደ ሶስተኛ ወገኖች ከማስተላለፍ በስተቀር የንብረት ባለመብት በሕግ ዕውቅና የተሰጡት ሥልጣኖች ይኖሩታል፤

ሠ/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) ድንጋጌ ቢኖርም የተያዘውን ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል መያዣ ለማድረግ ወይም ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ይህንኑ ተግባር የመፈጸም ሥልጣን እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) (ሠ) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻን ወይም በአንቀፅ 34(4) መሰረት የሚቀርብ ሪፖርትን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን እና የሚቻል በሆነ ጊዜ የንብረቱን ባለመብት አስተያየት ከሰማ በኋላ ጥያቄውን በመቀበል እንዲፈጸም ለማዘዝ፣ ለማሻሻል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል፤

3) የመንግስትም ሆነ የግል ተቋም ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ንብረት ለማስተዳደር ሥልጣን ለተሰጠው የንብረት አስተዳዳሪ የስራ ግዴታውን ለመወጣት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 34. የንብረት አስተዳዳሪው ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 31 መሰረት የሚሾም ንብረት አስተዳዳሪ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡

1) እንዲያስተዳድር የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ ኃላፊ ለመሆን የሚችል ዋስ ወይም መያዣ የመስጠት፥

2) ፍርድ ቤቱ በሚወስነው መሰረት ከንብረት ማስተዳደር የሚገኘውን ትርፍ ገቢ ማድረግ፥

3) በራሱ ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ ባደረገው ጉድለት በተረከበው ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነት የመውሰድ፤

Draft Confidential

4) ስለንብረቱ አያያዝ እና ስለተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች ለፍርድ ቤት በየሶስት ወሩ የሂሳብ መግለጫ እና ሪፖርት የማቅረብ፤

## 35.ስለ ንብረት አስተዳዳሪው ክፍያ

1) ፍርድ ቤቱ የንብረት አስተዳዳሪውን የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል፤

2) አገልግሎት ክፍያውን በመወሰን ሂደት ፍርድ ቤቱ የንብረቱን ባህሪ፣ የአስተዳደር ስራውን ክብደት፣ ለሥራው የሚያስፈልገውን የካፒታል መጠን፣ የሥራውን ውጤታማነት እና ሌሎች ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት የንብረት አስተዳዳሪውን፣ የዐቃቤ ሕግን እና የሚቻል በሆነ ጊዜ የንብረቱ ባለቤት አስተያየት በመስማት ይሆናል፡፡

## 36.ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ የዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት

1) ዐቃቤ ሕግ ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡

ሀ/ የንብረት አስተዳዳሪ እንዲሾም ወይም እንዲሻር ማመልከቻ የማቅረብል፤

ለ/ የሚያዘውን ንብረት ከሶስተኛ ወገን ነጻ በማድረግ ለንብረት አስተዳዳሪው የማስረከብ፤

ሐ/ የዕግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ማንኛውንም አይነት ንብረት በተመለከተ መደበኛ የጉብኝትና ቁጥጥር ስራ የመስራት፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሐ) የተደነገገውድንጋጌ ቢኖርም እንደየአስፈላጊነቱ ዐቃቤ ሕግ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት እስከ ምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ሳያስፈልገው ድንገተኛ ጉብኝት እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል:

Draft Confidential

3) ዐቃቤ ሕግ በሚያደርገው መደበኛም ሆነ ድንገተኛ ጉብኝት የሚያገኘው ጉድለት በተለመለከተ አስተዳዳሪው እርማት ከማድረግ ጀምሮ አስተዳዳሪ እንዲቀየር የሚጠይቅ ማመልከቻ ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 37.የተወረሰ ንብረት አጠቃቀም

1) አግባብነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ከተወረሰ ንብረት ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፡፡

2) የሚወረሰውን ገንዘብ ወይም ንብረትን በተመለከተ ተጎጂ ሲኖር ከወንጀል የተገኘው ንብረት በአይነት በተገኘ ጊዜ ለተጎጂው የሚመለስ ሲሆን ተለውጦ፣ ተላልፎ ወይም ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የደረሰው ጉዳት ትክክለኛ ዋጋ በብር ይከፈለዋል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ለተጎጂው የሚመለሰው ንብረት እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጎጂው ከሚከፈለው ንብረት የሚተርፍ ንብረት ይወረሳል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም በአይነት የተወረሰ ንብረት የፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ለሚሳተፉ አካላት ማጠናከሪያ ይውላል፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት ለፍትህ ስርዓቱ ማጠናከሪያ የሚውለው ንብረት አጠቃቀም በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፤

6) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እና በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሰረት የተቋቋመው የተጎጅዎች ፈንድን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

Draft-Confidential

## ክፍል ሰባት

## ስለ ንብረት ማስመለስ ዓለም ዓቀፍ ትብብር

### 38. ጠቅላላ

1) ሚኒስቴሩ ለዚህ አዋጅ አላማ ሲባል የዓለም አቀፍ የትብብር ማዕከላዊ ባለስልጣን ነው፤

2) ንብረት ማስመለስን በሚመለከት በጋራ ወይም በተናጠል ምርመራ የማድረግ፣ ንብረቶችን የመያዝ ወይም የማገድ፣ ለማስተዳደር፣ በጥፋተኝነት ላየ የተመሰረተ ወይም በጥፋተኝነት ላይ ባልተመሰረተ ንብረት ለመውረስ፣ ለማስመለስና ለፍርድ በማቅረብ ረገድ ከሌሎች ሀገሮች አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት ለሚቀርብ የትብብር ጥያቄ ሚኒስቴሩ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት የጋራ የሕግ ድጋፍ ትብብር ማድረግ አለባቸው፡፡

### 39. የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ

1) የንብረት ማስመለስን በሚመለከት የጋራ የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በሌላ ሃገር አመልካችነት ሲቀርብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት ይስተናገዳል፤

2) የንብረት ማስመለስን በተመለከተ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፣

ሀ/ ንብረቱን በተመለከተ ከሰዎች ማስረጃ ወይም ቃል መቀበልን፤

ለ/ የተያዙ ሰዎችን ወይም ፍቃደኛ የሆኑ ምስክሮችን ማስረጃ እንዲሰጡ ወይም ምርመራውን እንዲረዱ ለጠያቂው አገር የዳኝነት አካላት ማቅረብን፤

ሐ/ የፍርድ ቤት ሰነዶችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ማድረግ፤

መ/ የፍተሻ፣ የመያዝ ወይም የማገድ ሌሎች ጊዜያዊ እርምጃዎችን ማስፈጸም፤

ሠ/ መረጃዎችን፣ የማስረጃ ቁሳቁሶችንና የባለሙያ ግምቶችን መስጠት፣

Draft Confidential

ረ/ የመንግስት፣ የባንክና የፋይናንስ፣ የተቋማት ወይም የንግድ ስራ መዝገቦችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችንና መዝገቦችን ዋና ወይም የተረጋገጡ ቅጅዎችን መስጠት፤

ሰ/ የወንጀል ፍሬን፣ የወንጀል መፈጸሚያዎችን፣ ለወንጀል መፈጸሚያነት ለመዋል የታሰበ ንብረት፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማስረጃነት ወይም ለመውረስ ዓላማ ተከታትሎ መለየትን ወይም ማግኘትን፣

ሸ/ ንብረት መውረስን ወይም ማስመለስን፤

ቀ/ ሌሎች ከኢትዮጵያ ሕጎች ጋር የማይቃረኑ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄዎችን፡፡

## 40. የምርመራ ስራን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

1) አግባብነት ያለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ጋር የማይቃረን ለየት ያለ ሥርዓት ተከትሎ እንዲፈጸም ካልተጠየቀ በስተቀር ምርመራው የሚካሄደው በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገገውን የሕግ ሥርዓት ተከትሎ ነው፤

2) የጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለስልጣን የመደበው የመንግስት ሃላፊ የምርመራ ሥራውን አፈጻጸም እንዲታዘብ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## 41. ጊዜያዊ እርምጃዎች መውሰድን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

1) በጠያቂው አገር እንዲወሰዱ የተጠየቁ ጊዜያዊ እርምጃዎች አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚፈጸሙ ሲሆን እንዲወሰዱ የተጠየቁት እርምጃዎች በጥቅል አነጋገር የተገለጹ ከሆነ እና በህጉ የተደነገጉትና ይበልጥ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

2) የተጠየቁ እርምጃዎች በኢትዮጵ ሕግ የተደነገጉ ካልሆኑ አግባብ ያለው ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉት እና በውጤት ይበልጥ ቅርበት ያላቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡

Draft-Confidential

3) ጊዜያዊ እርምጃዎችን ስለማንሳት በዚህ አዋጅ የተደነገገው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ሆኖም እርምጃዎቹ እንዲነሱ ከመደረጋቸው በፊት አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## 42. የመውረስ እርምጃን የሚመለከት ድጋፍ ጥያቄ

1) የንብረት መውረስ ትእዛዝ እንዲፈጸም የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ ሚኒስቴሩ በጠያቂው አገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው ውሳኔ እውቅና ሰጥቶ ማስፈጸም ወይም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የመውረስ ትዕዛዝን እውቅና በማሰጠት ጉዳዩን ማስፈጸም አለበት፡፡

2) በጠያቂው ሃገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው የመውረሻ ትእዛዝ እውቅና ተሰጥቶ የሚያስፈጽም ከሆነ ትዕዛዙ የተመሰረተበትን የማስረጃ ግኝቶች እንዳለ ወስዶ ማስፈጸም አለበት፡፡

3) የንብረት መውረስ ትዕዛዙ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት የሚሸፈን እና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ንብረትን የሚመለከት መሆን አለበት፡፡

Draft-Confidential

## 43. የመገናኛ ቋንቋ

1) የሕግ ድጋፍ ትብብር ጥያቄ እንዲሁም ደጋፊ ሰነዶች በጽሁፍ ተደርገው በፌደራል ቋንቋ መቅረብ አለባቸው፡፡

2) አስቸኳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ጥያቄ በቃል ሊቀርብ ይችላል፤ ሆኖም ግን አስፈላጊ ነገሮችን የሚያሟላ የጽሁፍ ጥያቄው በአስር ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

## 44. ከአንድ በላይ በሆኑ ሃገሮች የጋራ ትብብር ድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ

በተመሳሳይ ንብረት ላይ የጋራ የሕግ ድጋፍ ጥያቄ ከአንድ በላይ በሆኑ አገሮች ሲቀርብ በመጀመሪያ የሁለትዮሽ ስምምነት ያላቸው አገራት፣ በመቀጠል በዓለም አቀፍ የጋራ ስምምነት መሰረት በመቀጠል የእንካ ለእንካ ስምምነት ያላቸውን ሃገሮች ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

## 45. በሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ስለሚወጣ ወጪ

1. በስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር የትብብር ወጪ በትብብር ጠያቂ ሃገር የሚሸፈን ይሆናል፡፡
2. በኢትዮጵያ የሚጠየቅ ትብብር ወጭው በፌዴራል መንግስት ይሸፈናል፡፡
3. በኢትዮጵያ የሚሸፈን የትብብር ወጪ ክፍያ በፌደራል መንግስት የገንዘብ ሥርዓት እና የፋይናንስ ሕግ መሰረት ይወሰናል፡፡

## 46.የሕግ የጋራ ድጋፍ ጥያቄን ስለመከልከል

1) የሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ጥያቄ በሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊከለከል ይችላል፡

ሀ/ የቀረበው ጥያቄ በዚህ አዋጅ ወይም ሌሎች አግባብነት ባለቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ያልቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የቀረበውን የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ ማስፈጸም የኢትዮጵያን ሕግና ሥርዓት፣ ሉዓላዊነት፣ ደህንነት፣ የህዝብ ጥቅም፣ ሞራል ወይም ሌሎች መሰረታዊ ጥቅሞችን የሚነካ ከሆነ፣

ሐ/ ጥያቄው የቀረበበት የወንጀል ድርጊት በኢትዮጵያ ውስጥ በመዳኘት ላይ ከሆነ ወይም የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣

መ/ የትብብር ጥያቄው የቀረበው በግለሰቡ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ወይም ጾታ ላይ ብቻ ተመስርቶ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት ሲኖር፣

ሠ/ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተጠቀሰውን ወንጀል በሚመለከት የተጠየቀውን እርምጃ ወይም ተመሳሳይ ውጤት የሚኖረውን ሌላ እርምጃ መውሰድ የማይፈቀድ ከሆነ፣

Draft-confidential

ረ/ በውጭ ሃገር የተሰጠው ውሳኔ የተከሳሹን የመከላከል መብት በበቂ ደረጃ ባላስተናገደ ሁኔታ የተሰጠ ከሆነ፥

ሰ/ ትብብር የተጠየቀበት ንብረት እጅግ አነስተኛ ግምት የሚሰጠው ሲሆን፡፡

2) ሚንስቴሩ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበትን ምክንያት አግባብ ላው የጠያቂው አገር ባለስልጣን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 47.ንብረቱን ስለማስወገድ ወይም ለጠያቂው አካል ስለመመለስ

1) በጠያቂው አገር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ መሰረት የተወረሰ ንብረት በሚከተለው መልኩ ሊወገድ ወይም ወደ ጠያቂው አካል ሊመለስ ይችላል፡-

ሀ/ ከጠያቂው አካል ጋር በሚደረግ የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም በአለምዓቀፍ ስምነቶች መሰረት፣

ለ/ የሁለትዮሽ ስምምነትም ሆነ የአለምአቀፍ ስምምነት በሌለ ጊዜ ከጠያቂው አገር ጋር እንደየጉዳዩ በሚደረግ ስምምነት፤

2) የሚመለሰውን ንብረት በተመለከተ በተቀናጀና በጋራ የንብረት ማስመለሱ ያከናወኑ ከሆነ ንብረቱ የሚካፈሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ሚንስቴሩ በስምምነት ሊወስን ይችላል፡፡

3) የሚመለሰው ንብረት ጥሬ ገንዘብ በሆነ ጊዜ ጠያቂው አገር የባንክ ማስተላለፊያ ዝርዝር ሁኔታዎችን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

4) ንብረቱ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ በሆነ ጊዜ የንብረት መመለስ ሂደቱ ወይም የአወጋገድ ሂደቱ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

Draft-Confidential

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 48.ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ማበረታቻ

1) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት የሚመለስና የሚወረስ ንብረትን በሚመለከት ስለንብረቱ አመጣጥ እና የሚገኝበትን ሁኔታ በተመለከተ ጥቆማ በመስጠቱና በጥቆማው መሰረት ንብረቱ የተወረሰ እንደሆነ ዝርዝር አፈፃፀሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የጠቋሚ ክፍያ የሚከፈል ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ጥቆማ የሚሰጥ ሰው ማንኛውም የንብረት ምርመራን የማድረግ፤ መረጃ የመሰብሰብ ወይም ክስ የማቅረብ ስልጣን ያለውን ባለሙያ፣ ሃላፊን ወይም በሙያው አማካኝነት መረጃውን ያገኘ ማንኛውንም ሰው አያካትትም፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ከተካተቱት አካላት በተዘዋዋሪ የሰጠውን መረጃና ማስረጃ ይዞ ለሚቀርብ ሰው የጠቋሚ ክፍያ አይከፈለውም፡፡

### 49.የሥራ ክፍል ስለማደራጀት

1) ሚኒስቴሩ የንብረት ማስመለስ ምርመራ የሚያደርግ፥ ክስ የሚመሰርት እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን የሚያከናውን የስራ ክፍል ያደራጃል፥ የስራ ክፍሉ ዐቃቤ ሕግ፣ መርማሪ እና ሌሎች አስፈላጊ ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች ይኖሩታል፤

2) የስራ ክፍሉ በንብረት ማስመለስ ሂደት ውስጥ ተጠርጣሪን በመጥራት፣ በማቆየት፣ በብርበራ፣ በመያዝ፣ ንብረት በመውረስ፣ በማስተዳደር እና ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ከፖሊስ ተቋማት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በተደነገገው መሰረት የሚቀጠሩ መርማሪ እና ሌሎች አስፈላጊ ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በዐቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚተዳደሩ ይሆናል።

Draft-Confidential

## 50. ተጎጅዎች የንብረት ማስመለስ ክስ ስለሚያቀርቡበት ሁኔታ

1) በወንጀል የተገኘው ንብረት የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የሌላ ግለሰብ ንብረት ከሆነ ይኸው ቷቋም ወይም ግለሰበ በወንጀል የተገኘውን ንብረት እንዲመለስ በፍትሃ በሂር ክስ እንዲመሰርት ሚኒስቴሩ ፍቃድ ሊሰጥ ወይም ሊወክል ይችላል፤

2) ሚኒስቴር እንዚህ ተቋማት የሚመሰርቱትን ክስ በሚመለከት ውጤቱን ይከታተላል፡፡

## 51.የዳኝነት ሥልጣን

1) ለንብረት ማስመለስ ሂደቱ መነሻ የሆነው የተፈጸመው ወይም ተፈጽሚል ተብሎ የተጠረጠረውን  ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የንብረት ማስመለስ ክሱንም በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣን አለው፤

2) ንብረቱ ከወንጀል ድርጊት ጋር ባለው ግንኙነት የተነሳ በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት ማስመለስ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ለግንኙነቱ መነሻ የሆነውን ወንጀል የመዳኘት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የንብረት ማስመለስ ክሱንም በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ስልጣን አለው፡፡

3) ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በተመለከተ በፍትሃ-ብሔር ጉዳዮች የፍርድ ቤት ስልጣን መሰረት ይዳኛል፡፡

## 52.የወንጀል ተጠያቂነት

1) በዚህ አዋጅ መሰረት ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲገልጽ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ በሌሎች ሕጎች የበለጠ ቅጣት የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር ማስረጃውን እንዲያቀርብ ከመገደዱ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

2) ማስረጃ የተጠየቀው ሰው ማስረጃውን የደበቀ ፣ ሃሰተኛ ማስረጃ የሰጠ፣ ማስረጃውን ያጠፋ ፣ መረጃ መጠየቁን ሚስጥራዊነት ያልጠበቀ እንደሆነ

Draft-Confidential

በሌሎች ሕጎች የበለጠ ቅጣት የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

3) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት በንብረቱ ላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የእግድ፣ የመያዝ፣ የማስተዳደር ወይም የመውረስ ትዕዛዝ በመጣስ ትዕዛዙን የሚቃረን ማንኛውንም ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና በንብረቱ ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ያልተገባ ጥቅም በሚኖር ጊዜ በደረሰው ጉዳት ወይም በተገኘው ጥቅም ልክ ከ10% እስከ 15% በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ትዕዛዙ የተጣሰው የሕግ ሰውነት ባለው አካል በሆነ ጊዜ ከ20% እስከ 30% የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 53. ደንብና መመሪያን የማውጣት ሥልጣን

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ለማውጣት ይችላል፡፡

2) ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 54.የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

1) ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ እንደአግባብነቱ የፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን ብዜት በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1132/2010 እና የሽብርተኛ ሃብት የሚታገድበት ስነ ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 306/2006 ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

Draft-Confidential

## 55.የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

1) ለንብረት ማስመለስ ዓላማ ሲባል በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ የንብረት ማስመለስ፣ ማገድ፣ መያዝ፣ ማስተዳደርና እና መውረስን የሚመለከቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የአዋጅ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

ሀ/ የተሻሻለው የጸረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997፣

ለ/ የተሻሻለው የጸረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 882/2007፣

ሐ/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 780/2005፣

መ/ የሽብር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1176/2012፣

ሠ/ በሰው የመነገድና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012፣

2) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ እና ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 56.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የውርስ አቤቱታ ቀርቦባቸው በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች በነበረው የሕግ ሥርዓት መሰረት የሚታዩ ይሆናል፡፡

Draft-confidential

## 57.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ …… ቀን ….. ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

Draft-Confidential